

# የማያስተኛኝ እንባ





እና እንዲህ ነች ኢትዮጵያ ቀብሮ ወደ ቤት ምልስ፣
ደማችን ከንቱ ሆነ?  ብሎ ሲለኝ የሙታን ነብስ።
ሲያብከነክነኝ  ቁጭት እህህ ጠዋት ማታ፣
ሲያንቀጠቅጠኝ ምሬት አልሰጥህ ሲለኝ ፋታ፤
የምን መጠበብ እላለሁ የመንገድ ምርጫ ፍለጋ፣
ያለ ትግል ድል የለም ሳይጨልምም አይነጋ።
ዋይ ዋይ የሚል እሪታ ከዳር እዳር የሚያስተጋባ፣
ተነስ ደም መላሼ! የሚለኝ የእናት የእህቶቼ እንባ፤
እርሱ ነው የማያስተኛኝ እየኮሰኮሰ እየቆጠቆጠ፣
ልረፍ ያለውን ሰውነቴን በቁጣ በአመጽ እየናጠ።




እና እንዲህ ነች ኢትዮጵያ ቀብሮ ወደ ቤት ምልስ፣
ደማችን ከንቱ ሆነ?  ብሎ ሲለኝ የሙታን ነብስ።
ካፈራችን ማን ሊነቅለን የተዋሀድናትን በሞት፣
ይብላኝ እንጂ ለናንተ መቀበርያም ለምታጡት።
ሀገር እንደ አድባር ቂጣ ግራ ቀኝ ሲበትኑ፣
ምነውሳ መፍዘዛችሁ ይሉኛል እኮ ሙታኑ።
ሌት የሚቀሰቅሰኝ እስከመቼ የምለው መገፋት፣
የእናት የእህቶቼ እንባ ነው የወገኔ ጣር ጩኸት።
እናም የመንደር ፖለቲካ አርቲ ቡርቲውን ትቼ፣
የፈዘዘኝን ምትሀት የደነዘዘኝን ፍርሀት አጥፍቼ፤
ይህንን ምስጥ ይህንን ነቀዝ ከውስጤ ሳላጠፋ፣
እንዴትስ ነው የማሸልብ እንዴትስ ላንቀላፋ።





እና እንዲህ ነች ኢትዮጵያ ቀብሮ ወደ ቤት ምልስ፣
ደማችን ከንቱ ሆነ?  ብሎ ሲለኝ የሙታን ነብስ።
ምንኛ ነው ዝምታህ የሚያስቆዝም ዳር አቁሞ፣
መከራን ሸክፎ ሲጭንብህ በጎጥ ልጓም ለጉሞ።
ምነው መፍዘዝህ ይለኛል የሰማይ መጋረጃ ከፍቶ፣
እስኪወስድህ ነው መጠበቅህ የእንባው ጎርፍ ሞልቶ?
እውነትም ይህንን ተውሳክ የተጣባኝን ትላትልም፣
ከውስጤ ሲቦጠቡጠኝ ተንጋልዬ ከማስታምም።
አንዴ እንዲያሸረኝ ተግቼ እንቆቆም ይሁን ኮሶ፣
ያኔ አሸልብ ይሆናል ሳየው የልብ የሀሳቤ ደርሶ።
አሁን ግን የሚያንገበግበኝ በቁጭት የሚንጠኝ፣
የእናት የእህቶቼ እንባ ነው እንቅልፌን የሚነሳኝ።





ከ ትንሣዔ

ግንቦት 2000